ጥቅምት 26 ቀን 2006 ዓ.ም.

# በታላቋ ብሪታንያ ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን መንግሥት በነደፈው የቤቶች ልማት ፕሮግራም ለመሳተፍ እንዲችሉ በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤቶች ፈላጊዎች ምዝገባ ከህዳር 1 ቀን 2006 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2006 ዓ.ም. እንደሚካሄድ መገለጹ ይታወሳል::

ይሁን እንጂ የዳያስፖራው አባላት ከአዲስ አበባ ከተማ በተጨማሪ ድሬዳዋን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች የመኖሪያ ቤት እንዲኖሯቸው ዕድሉን ለመስጠት ሲባል የቤቶች ልማት ፕሮግራም ክልሎችን እንዲያቅፍ እንደተወሰነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል::

በዚሁ መሠረት በክልሎች የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ማስፈፀሚያ ረቂቅ መመሪያ ለማዘጋጀት በቂ ዝግጅት በማስፈለጉ በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤቶች ፈላጊዎች ምዝገባ በታቀደው መሠረት ህዳር 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ለመጀመር አልተቻለም:: ስለሆነም አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች ምዝገባው የሚጀምርበትን ቀን ወደፊት የምናሳውቅ መሆናችንን እንገልፃለን::

ከሠላምታ ጋር